# የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና ህዝቡን የማይመጥኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች

(አዲሱ አረጋ ቂጤሳ) 03/03/14

*መግቢያ*

በሃገራችን ዴሞክራያዊ ስርዓት ግንባታ ጉዳይ የህዝቡ የፖለቲካ ትግል መሰረታዊ አላማ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ለሃገራችን ልማትና ሰላም ቀጣይነት አማራጭ ሳይሆን የህልዉና ጉዳይ እነደሆነም በተደጋጋሚ ተወስቷል፡፡ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመራጩን ህዝብ መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ አማራጭ ፖሊሲ ሃሳቦቸን በማመንጨት፣ ያመነጬት ሃሳብ በህዝቡ እንዲሰርጽ ሰላማዊ የሀሳብ ትግል በማድረግና አመራር በመስጠት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት የማይተካ ሚና የሚጫወቱ የህዝብ አደረጃጀቶች ናቸዉ፡፡ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሱት ሀገራት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዜጎች ግልጽና የተተነተ ሃሳቦችን በማቅረብ በሚያደርጉት ብቃት ያለዉ ሃሳብ ትግል በሂደቱ ዉስጥ የመራጩን ህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ በማሳደግ፣በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የመንግስት ስልጣን በመያዝና አማራጭ ሃሳቦቻቸዉን ተግባራዊ በማድረግ የሚጠበቅባቸዉን ሚና በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ባለ ብዙ ቋንቋ፣ ብሄር፣ ባህል ወዘተ ትልቅ ሀገር፣ሕዝቦቿ ለዘመናት በጭቆናና በድህነት አረንቋ ሲሰቃዩ ለነበረች ሀገር፣ተቃዋሚ የፖቲካ ፓርቲዎች ካለቸዉ አቋም በመነሳት ስንመዝን የሚጠበቅባቸዉን ሚና የሚወጡ አይደሉም፡፡ በዚህች አጭር ጽሁፍ በኢትዮጵያ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት የሚታይባቸዉ የብቃት ጉድለት ለመዳሰስ ይሞከራል፡፡

1. ጽንፈኛ የፖለቲካ አቋም፣ የተቃዋሚዎች የብቃት ማነስ መገለጫ

የቀድሞዉ የኢዴፓ ፕሬዝደንት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የነበሩት የተከበሩ አቶ ልደቱ አያሌዉ የሃገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለሚያራምዱት ጽንፈኛ የፖለቲካ አቋም መድሎት በተሰኘዉ መጽሀፋቸዉ የሚከተለዉን ሃሳብ አስፍረዉ ነበር፡፡

> *“ በአገሪቱ የምንገኝ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለገዢዉ ፓርቲ እዉቅናና አክብሮት ከመስጠት ረገድ ተመሳሳይ የከረረ አቋም ነዉ የምናራምደዉ፡፡ ተቃዋሚዎች አንድ ጊዜ እንዲህ አይነቱን ለኢህአዴግ እዉቅናና አክብሮት የመንፈግ አቋም ለትግላችን የሚጠቅም አቋም አድርገን ስለወሰድነዉ ደጋፊዎቻችንንም በዚህ አይነት ጭፍን አስተሳሰብ ስለቀረጽናቸዉ ይህ የቆምንበት መሰረት እንዳይሸረሸርብን በመስጋት ኢህአዴግ የሚሰራዉን ስራ በሙሉ ጎጅም ይሁን ጠቃሚ በጭፍን ከመቃወም ወደኋላ የማንል የፖለቲካ ሃይሎች ሆነናል፡፡በእስካሁኑ የትግል ሂደት በተግባር እንደታየዉ*

> *እንዲህ አይነት የከረረ አቋም ያለን የፖለቲካ ፓርቲዎች ብሄራዊ መግባባትንና የመቻቻል ፖለቲካን መሰረት ያደረገ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በአገራችን እንዲገነባ የሚያስችል በጎ አስተዋጽኦ ሊኖረን አይችልም፡፡ እንዲያዉም እንዲህ አይነቱን ጭፍን ተቃዉሞ ዓላማዉ ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲ ሊኖረዉ የሚችለዉ ሚና በተቃራኒዉ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት መሆን ነዉ፡፡" (መድሎት፡2002 ገጽ 12)*

ዛሬም ቢሆን የሀገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆነ ደጋፊዎቻቸዉ ከጽንፍ ፖለቲካ አልተላቀቁም፡፡ በማህበራዊ ድረ ገጾች እንኳ ስድብ፣ሽሙጥ፣ጥላቻ መናናቅና የመመሳሰሉትን ተራ ነገሮችን ከመርጨት ባለፈ ጠቃሚ ሃሳብ ሲያመነጩና በሃሳብ ዙሪያ ሲሞግቱ አይታዩም፡፡ ገዢዉን ፓርቲ ማክበርና እዉቅና መስጠት  ቀርቶ እርስ በርስ እንኳ አይደማመጡም፡፡ እርስ በርሳቸዉ ተስማምተዉ ማደር የማይችሉ  በመካከላቸዉ የሚፈጠረዉን የሃሳብ ልዩነት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ብቃት የሌላቸዉ ሃይሎች ናቸዉ፡፡ በምርጫ 2002 የዕጩ ተወዳደሪዎች ዝግጅት ወቅት ሁለት የመድረክ  አባላት የሆኑ ግለሰቦች መደማመጥ አቅቷቸዉ በቦክስ ሲቃመሱ አይተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ መድረክ አንድነት የተባለዉን አባል ድርጅቱን ማገዱን ሰምተናል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነዉ ከጽንፈኝነት የተነሳ ሀሳብን በሃሳብ የማሸነፍ፤ ልዩነትን በዴሞክራሲያዊ አካሄድ የመፍታት ብቃት ስላላዳበሩ ነዉ፡፡ ከዚህም የተነሳ የሃገራችን ተቃዋሚዎች አሁን በያዙት ጽንፈኛ ፖለቲካ አቋም  አገር ለመምራት ብቃት የሌላቸዉ፤ አሁን የተፈጠረዉን  እድገት  ፈላጊ ህብረተሰባችንን ለመምራት የማይመጥኑ ሃይሎች ናቸዉ፡፡

2. ህዝቡን የማይመጥን ፖለቲካዊ ዲሲፒልን፤ የተቃዋሚዎች ብቃት ማነስ መገለጫ

የሃገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያራምዱት ጽንፈኛ አቋም  ባሻገር እጅግ በጣም ደካማ የሆነ ተቋማዊ  ባህል እና የተበላሸ ግለሰባዊ ዲሲፕሊን ዉስጥ እንደከታተቸዉ ክቡር አቶ በረከት ስምኦን  የሁለት ምርጫዎች ወግ በተሰኘዉ መጽሃፋቸዉ እንደሚከተለዉ ገልጸዉታል፡፡

> *"እነርሱ ሁሌም ባጭሩ ተዘጋጅተዉ ባጭሩ ይሮጣሉ፡፡ተመረቁ ቢሏቸዉ ሲፈጠሩ ጀምሮ ረጅም ነገር አይወዱም፡፡ቁምነገር የሚመከርበት ረጅም ስብሰባ ይጠላሉ፡፡ እንደኢህአዴግ ረጅም ጊዜ ወስደዉ ተጨንቀዉና ተጠበዉ ዘላቂነት ያለዉ ስራ መስራት አይችሉም፡፡ ነገር ሲረዝም በጣም ያሰለቻቸዋል፡፡ እናም ነገረ ስራቸዉ ሁሉ ጥድፊያ በዛበት ነዉ፡፡ስብሰባቸዉም ጭምር፡፡ ሲጣሉም ሆነ ሲስማሙ ፣ሲፋቱም ሆነ ሲጋቡ ቅጽበት አይወስድባቸዉም፡፡ኢትዮጵያን የምታክል ትልቅ ሀገር  በትንሹ በማሰብ በትንሹ በመዘጋጀትና በትንሹ  በመስራት ልትመራ ትችላለች ብለዉ ያምናሉ፡፡ ስለዚህም ዝግጅታቸዉ  ሁሌም አጭርና ዉሽልሽል  ያለ ነዉ፡፡ ራሳቸዉን ለትልቅ ሀላፊነት ሲያጩም በተገቢዉ አይዘጋጁም፡፡ የነእከሌ ቅንጅት፣ የነእከሊት ህብረት ወይም የነእከሌ ጥምረት ብለን የጥቂት ዶክተሮች ስም ካስገባን በቂያችን ነዉ፡፡ማንኛዉንም ነገር እዚህ አዲስ አበባ ላይ ተቀምጠን እንጨርሰዋለን ባይ ናቸዉ፡፡ገጠር ወርዶ፣ ገበሬን አሳምኖ ህዝብን ከነርሱ ጎን የማሰለፍ ትዕግስቱ የላቸዉም፡፡ሸገር ላይ ሆነዉ የማዳበሪያ ዋጋ ተወደደ ካሉ አርሶ አደሩ ሁሉ ህዝበኛ መፈክራቸዉን ተቀብሎ በመንግስት*

*ላይ የሚነሳ ይመስላቸዋል፡፡ በየኢምባሲዉ እየዞሩ የኢህአዴግን ስም በማጥፋት እርሱም የሚያበቃለት እነርሱም ለስልጣን የሚቃረቡ መስሎም ይታያቸዋል፡፡" (በረከት፣2003፣197)*

ከላይ የሁለት ምርጫዎች ወግ ከተሰኘዉ መጽሃፍ የተዋስኩት አንቀጽ የሃገራችንን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢትዮጵያን የምታክል ታላቅ ሃገር የማስተዳደር ብቃት እንዴሌላቸዉ ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነዉ፡፡ የሃገራችን ፖለቲካ መለስ ብለን በመንቃኝበት ጊዜ ታሪካቻን የብሄር እና የሃይማኖት ጭቆና ታሪክ እንደነበር፣ በርስ በርስ ጦርነትና በፖለቲካዊ አለመቻቻል መተላለቅ የሰፈነበት ታሪክ እንደነበረ የድህነት፤የረሃብና የቸነፈር የሰቆቃ ታሪክ ወዘተ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከጂኦፖለተካዉም አንጻር አለም ላይ አደገኛዉ ቀጠና ተብሎ በተፈረጀዉ የአፍሪካ ቀንድ የምንገኝ ህዝቦች ነን፡፡ ይህን የመሰለ ታሪካዊ ዳራ ያላትን ሀገር እጣ ፈንታ ለመወሰንና ስልጣን አግኝቶ የሀገሪቱን ህዝብ በመምራት ኢትዮጵያን ከድህነት ቀንበር አላቅቄ፣ ሰላሟን አስፍኜ፣ ብልጽግናን አመጣለሁ የሚል የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ከምንም በፊት እነዚህን ከባድ ተልዕኮዎች መሸከም የሚያስችሉት ብቃት ያለዉ ድርጅታዊ ቁመናና ተቋማዊ ባህል፣ ከብረት የጠነከረ የአመራርና የአባላት ዲሲፕሊን መገንባት ህዝባዊነትን መላበስና ከህዝቡ ጋር መስራት ይጠበቅበታል፡፡

አሁን ባለዉ ተጨባጭ ሁኔታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀገር የመምራት ሀላፊነት ቢሰጣቸዉ በአጭር ሩጫ አስተሳሰባቸዉ የተጀመረዉን የልማት ጉዞ ማስቀጠል አይችሉም፡፡ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፣ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን በመገንባት ህዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ ወገብ የሚጎብጥ ከባድ ተልዕኮ እንደመሆኑ ጥብቅ ዲስፕሊንና ቁርጠኛ አመራር የሚጠይቅ በመሆኑ ይህን የመፈጸም ብቃት የላቸዉም፡፡ በደካማ ዲሲፒሊን በአስር ሺህዎች ኪሎሜትር የሚቆጠር የመንገድ ፕሮጀክቶችን ማስፈጸም አይቻልም፡፡ የህዳሴዉን ግድብ ፕሮጀክት ማስፈጸም አይቻልም፡፡ በሺህ ኪሎሜትሮች የሚቆጠር የባቡር ኔትዎርክ መዘርጋት አይቻልም፡፡ ሃገርን ከአልሸባብ፣ከሻዕቢያና ከጀሌዎቹ ጥቃት መከላከል አይቻልም፡፡ መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲን ማስፈን አይቻልም፡፡ ብዝሃነትን ማስተናገድ አይቻልም፤ ወዘተ ወዘተ፡፡ በአጠቃላይ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች አሁን ያላቸዉ ፖለቲካዊ ዲሲፒለን የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት ስለማይመጥን ራሳቸዉን በመፈተሽ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታዉ ብቁ ሆነዉ መቅረብ መቻል አለባቸዉ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንቅፋት መሆናቸዉ የማይቀር ጉዳይ ነዉ፡፡

### 3. ያለ አማራጭ መቃወም፤ ያለ አላማ አንድነት መዋሃድ፤የተቃዋሚዎች የብቃት ማነስ መገለጫ

በሀገራችን የሚገኙ አንዳንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝቡ የሚበጅ ግልጽ የፖለቲካ ፕሮግራም በመንደፍ አማራጭ ፖሊሲና ስትራቴጂ ከማቅረብ ይልቅ የገዥዉ ፓርቲ የአፈጻጸም ክፍተቶችና ድክመቶች ላይ በማተኮር የህዝቡን ስሜት ለመኮርኮር ይጥራሉ፡፡ የአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች አማራጫቸዉን ለህዝቡ እንዲያቀርቡ በሚጠየቁበት ጊዜ ለጊዜዉ አማራጭ

ፖሊሲ እንደሌላቸቸዉ ተመርጠዉ ስልጣን ከያዙ በኋላ ፖሊሲ እንደሚቀርጹ በድፍረት በአደባባይ ይናገራሉ፡፡

በሌላ በኩል ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በተለያዩ ጊዜያት ቅንጅት፣ ግንባር፣ ህብረት፣ ጥምረት ወዘተ በመፍጠር ለመታገል ተንቀሳቅዋል፡፡ በተበታተነ መልኩ ከመንቀሳቀስ ይልቅ ተደራጅተዉ በጋራ መታገል ክፉት የለዉም፡፡ ክፉቱ  የመተባበራቸዉ ዋነኛዉ ማዕከል የአላማ አንድነት ሳይሆን ባላቸዉ ጽንፈኛ የፖለቲካ አቋም ገዥዉን ፓርቲን የጋራ ጠላት አድርገዉ ስለሚወስዱና የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነዉ በሚል ፍልስፍና የሚተባበሩ መሆኑ ነዉ፡፡ የትብብር መመዘኛዉ ተቃዋሚ መሆን ብቻ በመሆኑ ህብረ ብሄራዊ አደረጃጀትን የሚከተለዉ ብሄራዊ አደደጃጀት ካለዉ፤ የትምክህት አስተሳሰብ አራማጁ  ከጠባብ ብሄርተኛዉ፤ የሊብራል ዴሞክራሲ ርዕዮተ አለምን የሚከተለዉ ሶሻል ዲሞክራሲን ከሚከተለዉ፣ የፖለቲካ ፕሮግራም ያለዉ የፖለቲካ ፕሮግራም ከሌለዉ ወዘተ እንደለማኝ እህል በአንድ ስልቻ ተቀላቅለዉ  ወደ ትብብር ይገባሉ፡፡  ትብብሩ ከመፈጠሩ የሊቀመንበርነት፣ የምክትል ሊቀመንበርነት እና የጸሃፊነት የሀላፊነት ድልድል የቅሬታ፣የኩርፊያና፣ የሽኩቻ መነሻ ይሆናል፡፡  ከዚያም የፖለቲካ አስተሳሰብን ወደ ማራመድና አቋም ወደ መዉሰድ ሲገባ በቡድን ወደመከፋፈል ያመራል፡፡ የእነ እከሌ የነእከሊት ቡድን መባባል፣ በጠባብና በትምክህኝነት ወዘተ መዘላለፍ፣ ይጀመራል፡፡ ገለልተኛዉ ጫፍ በሁለት ጫፍ ተቧድዉ የተኮራረፉትን በማስታረቅ ይጠመዳል፡፡ አንደኛዉ ሌላኛዉን ከዉህደቱ/ ከግምባሩ/ከቅንጀቱ/ከህብረቱ ሌላኛዉን የሚያስወግድበትን ወጥመድ በማዘጋጀት ይወጠራል፡፡ በዚህ ጤናማ ባልሆነ የዉስጠ ድርጅት ፖለቲካ የተነሳ ህዝቡን ሊጠቅም የሚችል የረባ  የፖሊሲ አማራጭ ሳይነደፍ ጊዜዉ ይሄዳል፡፡ በመጨረሻም ትብብሩ ይፈርሳል፡፡ ከዚያም እንደተለመደዉ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል ገዢዉ ፓርቲ ሊያሰራን አልቻለም ወደሚል ዉንጀላ ይገባል

4. ከሀገራዊ አጀንዳዎችን መቃወም የተቃዋሚዎች የብቃት ማነስ መገለጫ

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጠቃሚ ሀገራዊ አጀንዳዎችን ሃሳቦቹን ገዢዉ ፓርቲ ስላመነጫቸዉ ብቻ ኢ-ምክኒያታዊ በሆነ መንገድ ሲቃወሙ ሲያጥላሉ ተስተዉለዋል፡፡ ከጥቂት አመታት በፊት ራሱን የሶማሊያ የኢስላማዊ ፍርድቤቶች ህብረት ብሎ የሚጠራ አክራሪ ቡድን ሀገራችን ላይ ጂሃድ በማወጁ ገዢዉ ፓርቲ ራሳችንን መከላከል አለብን ብሎ  ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዉሳኔ ሃሳብ ሲያቀርብ ከኢዴፓ በስተቀር ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች -ኢ-ምክንያታዊ ተቃዉሞአቸዉን አራምደዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅዱን፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ወዘተ የገዢዉ ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ስልቶች ናቸዉ በማለት ሲቃወሙት ታይተዋል፡፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች  ብቃት ቢኖራቸዉ ኖሮ በሃገር ሉዓላዊነት የተቃጣን አደጋ መመከትና ህዝቡን ከድህነት የሚያላቅቁ ሀሳቦች በማንኛዉም አካል ሲቀርቡ ሃሳቦቹን ከማጥላላትና ከመቃወም በፊት ከህዝብ ጥቅም አንጻር ገምግመዉ አቋም  መዉሰድ ነበረባቸዉ፡፡ ሃሳቦችን ከህዝብ ጥቅም አንጻር እየመዘነ  አቋም የማይወስድ የፖለቲካ ድርጅት ሀገርን ለመምራት አይመጥንም፡፡

ማጠቃለያ

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አማራጭ ሃሳቦችን በማመንጨት በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የማይተካ ሚና እንዳላቸዉ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ከጽንፈኛ የፖለቲካ አቋም አቋም በመላቀቅበ መደማመጥና በመከባር ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባህልን ለማዳበር ካልተንቀሳቀሱ በጽንፈኛ አስተሳብ ሀገርን መምራት የሚታሰብ አይሆንም፡፡ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ተከታዮች ያሏቸዉ ግለሰቦች እንደመሆናቸዉ ቢያንስ ለተከታዮቻቸዉ አርአያ መሆን አለባቸዉ፡፡ በተጨባጭ በሚያሳዩት ህዝቡን የማይመጥን ፖለቲካዊ ዲሲፒልን የሚቀጥሉ ከሆነ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታዉ ምንም ገንቢ አስተዋጽኦ ሳያበረክቱ ይቀራሉ፡፡ የሃገራችን ተቃዋሚዎች ግልጽ የሆነ የፖሊሲ አማራጭ እና ጠንካራ አደረጃጀትዘዉ መቅረብ ካልቻሉ ያለፖሊሲ አማራጭ እና ኢህአዴግን በማጥላላት ላይ በተመሰረተ ወዳጅነት ሃገርን የሚያክል ነገር መምራት አይችሉም፡፡